**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ**

**SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA**

| | | |
|---|---|---|
| 1ki Diro Kiiro 15<br><br>Hawaasa, Dotteessa 25, 2013 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho<br><br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲፭<br>ሀዋሳ፣ ሚያዝያ ፳፭ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም |

**Amado**

**Wodhote Kiiro 15/2013**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Qoqqowu Mereershi Uurrinshubbara Mannu Wolqa Uurrinshu Gaamate Fultino Wodho ……… Qoola ….**

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፲፭/፳፻፲፫**

**በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በክልል ማዕከል ተቋማት የሰው ኃይልን በቋሚነት ለመመደብ የወጣ ደንብ ………… ገጽ…**

**Wodhote Kiiro 15/2013**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Qoqqowu Mereershi Uurrinshubbara Mannu Wolqa Uurrinshu Gaamate Fultino Wodho**

Itophiyu Federaalete Dimokiraasete Rippubilike Bayriidi Seeri garinni tantanantino Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimmara seerunni uurritinoti Qoqqowu mereershi mootimmate uurrinshubbara Qara Loosu Soorro /BPR/ xiinxallo assatenni kalaqantanno tantanora mannu wolqa gaamme loosu giddora eanno gede assa hasiissinnohura;

**ደንብ ቁጥር ፲፭/፳፻፲፫**

**በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በክልል ማዕከል ተቋማት የሰው ኃይልን በቋሚነት ለመመደብ የወጣ ደንብ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት መሠረት በተደራጀው በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሕግ በተቋቋሙ የክልል ማዕከል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት በማድረግ ለተፈጠሩ አደረጃጀቶች የሰው ኃይል መድቦ ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ በማስፈለጉ፤

**Mittu Waagi ….**
*ያንዱ ዋጋ*

AFFINI GAAZEEXI P.S.K …..
አፍኒ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. …..
Web address: www.affinigazet.gov.et

Wole widoonni Sidaamu Dagoomu Qoqqowira konni albaanni yannate geeshshira gaamooshshe afi'rino mannino ikko wodiidi qoqqowira keeshshitu loosaasine qoqqowinkera Qara Loosu Soorro /BPR/ xiinxallonni kalaqantanno loosu basubbara heewisiisatenni uurrinshunni gaama hasiissinohuranna ha'rinshono seerunni massagama noosehura,

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Jeefisiisaanote Amaale Mini Qoqqowu Bayriidi Seeri quwa 57 cinaancho quwa 6 hunda uynoonnisi biilloonyinni garinni tenne Wodho Fushshino.

**1. Harancho Su'ma**

Tenne wodho "Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Qoqqowu Mereershi Uurrinshubbara Mannu Wolqa Uurrinshu Gaamate Fultino Wodho Kiiro 15/2013" yine woshshinara dandiinanni.

**2. Tiro**

Qaalu horo wole tiro uytannota ikka hoogguro tenne wodho giddo፡

1. **"Qoqqowo"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowooti.
2. **"Albi Qoqqowo"** yaa Wodiidi Daga, Dagoominna Manni Qoqqowooti.
3. **"Albi Zoone"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma kalaqantara albaanni Sidaamu Daga Gashshootu Mereersha ikkite albi qoqqowinni kalaqante keeshshitinonna Ella 27/2012 M.D hanaffe ikkitotenni /by

በሌላ በኩል በሲዳማ ብሔራዊ ክልል ከዚህ ቀደም በጊዜያዊነት ምደባ ያገኙ ሰዎችም ሆነ በደቡብ ክልል የቆዩ ሠራተኞች በክልላችን በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት በሚፈጠሩ የሥራ መደቦች በማወዳደር በቋሚነት መመደብ በማስፈለጉና አሠራሩም በሕግ መመራት ስላለበት፣

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፯ ንዑስ አንቀጽ ፮ ላይ በተሰጠው ሥልጣን መስረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**፩ አጭር ርዕስ**

ይህንን ደንብ "በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በክልል ማዕከል ተቋማት የሰው ኃይልን በቋሚነት ለመመደብ የወጣ ደንብ ቁጥር ፲፭/፳፻፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪ ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩ "ክልል" ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፡፡

፪ "ነባሩ ክልል" ማለት የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ነው፡፡

፫ "የቀድሞ ዞን" ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ከመቋቋሙ በፊት የሲዳማ ሕዝብ የአስተዳደር ማዕከል ሆኖ በነባሩ ክልል ተመስትሮ የቆየና ከሰኔ ፳፺/፳፻፲፪ ዓ.ም ጀምሮ በተግባር/by conduct/ የፈረሰ የመንግሥት አስተዳዳር

conduct/ diigantino mootimmate gashshootu taqqaati.

4. **“Mootimmate Loosu Mine”** yaa seeru mannimma afidhe lallawunni woy wodhotenni mootimmate sokkara uurritinonna faynaansete buichose wo’munni wo’ma woy bocunni mootimmatenni gaammanni bajeettenni galtanno uurrinshaati.
5. **“Mootimmate Loosaasincho”** yaa qoqqowu hattono albi Qoqqowi Mootimmate Loosu Minna giddo uurrinshunni woy yannate geeshshira loosoho qaxarame woy gaamame loosanni keeshshino kalaqamu manchoti.
6. **“Gaamooshshe”** yaa mitte mootimmate uurrinshara loosanno loosaasincho Qoqqowu Mootimma loosu minnara Qara Loosu Soorro/BPR/ xiinxallonni kalaqamanno loosu baychira heewisamatenni qeele gaamame loosanno gede assate.
7. **“Labbanno Sekitere”** yaa seerunni uynoonni sokkanni mimmito labbanno qoqqowohonna albi qoqqowira heedhanno mootimmate uurrinshaati.
8. **“Biiro” woy “Biirote Sooreessa”** yaa aantensa garinni Dagitte Owaantenna Mannu Jiro Latishshi biirootinna sooreessaati.

### 3. Koo-teemmate Xawishsha

Tenne wodho giddo mitte koo-teemmanni xawinsoonni hedo wole koo-teemmano hanqaffanno.

እርከን ነው፡፡

፬ “የመንግሥት መሥሪያ ቤት” ማለት የሕግ ሰውነት ኖሮት በአዋጅ ወይም በደንብ ለመንግሥት ተልዕኮ የተቋቋመና የፋይናንስ ምንጩ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በመንግሥት በሚመደብ በጀት የሚተዳደር ተቋም ነው፡፡

፭ “የመንግሥት ሠራተኛ” ማለት በክልሉ እንዲሁም በነባሩ ክልል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ በመደበኛነት ወይም በጊዜያዊነት ተቀጥሮ ወይም ተመድቦ እየሠራ የቆየ የተፈጥሮ ሰው ነው፡፡

፮ “ምደባ” ማለት በአንድ የመንግሥት ተቋም ውስጥ እየሠራ ያለውን ሠራተኛ በክልሉ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት ለሚፈጠር የሥራ ቦታ በውድድር አሸንፎ ተመድቦ እንዲሠራ ማድረግ ነው፡፡

፯ “ተመሳሳይ ሴክተር” ማለት በሕግ በተሰጠው ተልዕኮ በክልሉና በነባሩ ክልል ያለ የመንግሥት ተቋም ነው፡፡

፰ “ቢሮ ወይም የቢሮ ኃላፊ” ማለት በቅደም ተከተላቸው መሰረት የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ቢሮ እና ኃላፊ ነው፡፡

### ፫ የጾታ አገላለጽ

በዚህ ድንብ ውስጥ በአንድ ጾታ የተገለጸው ሌላኛውንም ጾታ ያካትታል፡፡

**4. Jeefishshu Mami-geeshsha**

1. Tini wodho qoqqowu mereershi sekitere uurrinshubbara yannate geeshsha gaamante no hattono qoqqowu mootimmate gumulo garinni albi qoqqowira qoqqowu mereershi sekitere loosu minnara loossanni keeshshitino mootimmate loosaasine heewotenni qoqqowu mereershira uurrinshu gaamooshshe jeefisate loosu aana hossannoha ikkanno.
2. Tini wodho mootimmate loosaasine gashshootu lallawinni galtannonna lallawu gobbaanni addi wodhonni galtanno mootimmate loosu minnara loossanno loosaasine mitte yannara uurrinshunni gaamate loosu aana hossanno.
3. Konni quwi cinaanchu quwi 2 iima worroonnihu noo gedeenni hee'renna xaphoomu yoo mininna xaphoomu seeru allaalshi yooaanonna seeru allaalaano uminsa biddissinni gaantara dandiitanno.

**5. Gaamooshshe Jeefisate Ha'rinsho**

1. Qoqqowu loosu minnara yannate geeshsha gaamante noore ikko albi qoqqowi mereershira loosannonna qoqqowu mootimma gumulonni qoqqowu mereershira qara loosu soorro/BPR/ xiinxallonni kalaqantanno tantanora labbanno sekitere loosu minnara taalo woy mitteenni heewisante qeelatenni afidhanno loosu madawera gaamantannoha ikkanno. Tittiro biddissunni xawinsanni.
2. Konni quwi cinaanchu quwi 1 iima woroonni

**፬ የተፈጻሚነት ወሰን**

፩ ይህ ደንብ በክልል ማዕከል ሴክተር መስሪያ ቤቶች በጊዜያዊነት ተመድበው ያሉ እንዲሁም በክልል ምንግሥት ውሳኔ መሰረት በነባሩ ክልል በክልል ማዕከል ሴክተር መሥሪያ ቤቶች እየሠሩ የቆዩ የመንግሥት ሠራተኞች በውድድር በክልል ማዕከል ቋሚ ምደባ ለመፈጸም ሥራ ላይ የሚውል ይሆናል፡፡

፪ ይህ ደንብ በመንግሥት ሠራተኞች አዋጅ በሚተዳዳሩና ከአዋጁ ውጭ በልዩ ደንብ በሚተዳደሩ በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚሠሩ ሠራተኞችን ለአንድ ጊዜ በቋሚነት ለመመደብ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ዳኞችንና ዐቃቤያነ ሕግ በራሳቸው መመሪያ ሊመደቡ ይችላሉ፡፡

**፭ ስለምደባ አፈጻጸም ሂደት**

፩ በክልሉ መሥሪያ ቤቶች በጊዜያዊነት የተመደቡም ሆነ በነባሩ ክልል ማዕከል የሚሠሩና በክልሉ መንግሥት ውሳኔ በክልል ማዕከል በመሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ/BPR/ ጥናት መሠረት በሚፈጠር አደረጃጀት በተመሳሳይ ሴክተር መሥሪያ ቤት በእኩል ወይም በጋራ በመወዳደር አሸንፈው በሚያገኙት የሥራ መደብ የሚመደቡ ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይገለጻል፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተደነገገው

garinni albi qoqqowi qoqqowu mereershi sekitere uurrinshubbanni daganno heewisamaano qoqqowunniha loosu afoo dandiitannore ikka noonsa.

3. Kunni quwi cinaanchu quwi 1 iima worroonni garinni assinanni gaamooshshinni mitte labbanno sekitere loosu mini giddo madawe ajjannoha ikkeenna gaamantukkinni gattanno loosaasine biirote widoonni wole loosu minnara gaammanniha ikkanno. Tittiro biddissunni murranni.
4. Konni quwi cinaanchu quwi 3 iima worroonnihu noo gedenni hereenanni qoqqowu mereershi madaweha hooffayidi bikaancho wonsha hoogatenni woy madawe hoogenna gaamamikkinni gatannohu wonshanno madawe heedhanno gashshootu tantanora gaamamannoha ikkanno.
5. Gaamooshshe assinannihu biirotenni keenante deerra gumulleenna uurrinshunni manna gaamate fajjinoonni madabbara calla ikkanno.
6. Qoqqowu loosu minnara assinannihu uurrinshu gaamooshshe jeefinsi gedensaanni mannu wolqa looso ha’risate ajjannoha ikkiro hajo la’annonsa bissa gumultanno garinni biirote widoonni mittu mereershinni egensiishsha fushshinenna ikkado heewo assatenni mannu wolqa wonshinanniha ikkanno.

**6. Gaamooshshu Komite Uurrisa**

Qoqqowu mereershi mootimmate loosu minnara

መሠረት ከነባሩ ክልል ክልል ማዕከል ሴክተር ተቋማት የሚመጡ ተወዳዳሪዎች የክልሉን የሥራ ቋንቋ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ በተገለጸው መሠረት በሚደረግ ምደባ በአንድ ተመሳሳይ ሴክተር መሥሪያ ቤት ውስጥ መደቡ የሚያንስ ሆኖ ሳይመደቡ የሚቀሩ ሠራተኞች በቢሮው በኩል በሌሎች መሥሪያ ቤቶች የሚመደቡ ይሆናሉ፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፬ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የክልል ማዕከል መደብ ዝቅተኛ መስፈርት ማሟላት ባለመቻል ወይም መደብ ባለመኖሩ ሳይመደብ የሚቀር የሚያሟላው መደብ በሚገኝበት የአስተዳደር እርከን የሚመደብ ይሆናል፡፡

፭ ምደባ የሚደረገው በቢሮው ተመዝኖ፣ ደረጃ ተወስኖ በቋሚነት ለመመደብ በተፈቀደው መደብ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

፮ በክልል መሥሪያ ቤቶች የሚደረገው የቋሚነት ምደባ ከተፈጸመ በኋላ የሰው ኃይሉ ሥራውን ለማስኬድ የሚያንስ እንደሆነ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት በሚወስኑት መሠረት በቢሮው አማካይነት ከአንድ ማዕከል ማስታወቂያ ወጥቶ በቂ ውድድር በማድረግ የሰው ኃይሉ የሚሟላ ይሆናል፡፡

**፮ የምደባ ኮሚቴ ስለማቋቋም**

በክልል ማዕከል የመንግሥት መስሪያ ቤቶች

gaamooshshu looso jeefisate yannate geeshshi gaamooshshu komite mitte mittente uurrinsha giddo tenne wodhonni uurritino. Tittirsha biddissunni murranni.

**7. Koffeenyanna Kado**

1. Tenne wodho garinni assinanni gaamooshshi gumulo kaiminni kalaqamanno koffeenya buuxate looso loossanno yannate geeshshi komite mitte mittente qoqqowu mereershi loosu minna giddo tenne wodhonni uurritino. Tittirsha biddissunni murranni.
2. Konni quwi cinaanchu quwi 1 garinni uurritino komite uytino gumulonni koffi yaannohu shiqishi'ranno kado la'anno komite Dagitte Owaantenna Mannu Jiro Latishshi Biiro hundaanni galtannota ikkite tenne wodhonni uurritino. Tittirsha biddissunni murranni.
3. Konni quwi cinaanchu quwi 2 garinni uurritino komite uytanno gumulo gaamooshshu hajo lainohunni goofimarchu gumulo ikkitanno.

**8. Biddissa Fushshate Biilloonyi**

Tenne wodho loosu aana hosiisatenna gumulate biiro hasiisanno biddissanna bikaancho fushshitara dandiitanno.

**9. Reekkote Woro**

Tenne wodho garinni mannu wolqa gaamooshshe wo'munni wo'ma jeefinsa geeshsha qoqqowu mereerishi uurrinshubbara albiidi zoonera loosanni

ውስጥ የምደባ ተግባር የሚፈጽም ጊዜያዊ ኮሚቴ በእያንዳንዱ ተቋም ውስጥ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**፯ ቅሬታና ይግባኝ**

፩ በዚህ ደንብ መሰረት በተደረገ የምደባ ውሳኔ የሚፈጠር ቅሬታ የማጣራት ሥራ የሚሰራ ጊዜያዊ ኮሚቴ በእያንዳንዱ የክልል ማዕከል መስሪያ ቤቶች ውስጥ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሰረት በተቋቋመ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው የሚያቀርበውን ይግባኝ የሚያይና ተጠሪነቱ ለፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ቢሮ የሆነ ኮሚቴ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ መሰረት የተቋቋመ ኮሚቴ የሚሰጠው ውሳኔ የምደባ ጉዳይን በሚመለከት የመጨረሻ ይሆናል፡፡

**፰ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

ቢሮው ይህንን ደንብ ተግባራዊ ለማድረግና ለማስፈጸም መመሪያና መስፈርት ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፱ የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

በዚህ ደንብ መሰረት የሰው ኃይል ምደባው ሙሉ በሙሉ እስከሚጠናቀቅ በክልል ማዕከል ተቋማት በነባሩ ዞን ሲሰሩ የቆዩ

keeshitino mootimmate loosaasine yannate geeshsha gaamate fultino wodho kiiro 2/2012 garinni gaamante loosanni noo loosaasine yannate geeshsha gaamante noo uurrinsharanna madabera loosonsa suffannoha ikkanno.

**10. Jeefishshu Hee’rannosikki Seeranna Assoote**

1. Qoqqowu mereerishi uurrinshubbara albiidi zoonera loosanni keeshitino mootimmate loosaasine yannate geeshsha gaamate fultino wodho kiiro 2/2012 tenne wodhonni shaarantino.
2. Tenne wodho ledo kiphi yaanno aye seeri woy rosamino assooti tenne wodhonni hanqafantino hajubba lainohunni jeefishshu dihee’rannosi.

**11. Wodho Loosu Aana Hossanno Yanna**

Tini wodho Dotteessa 25/2013 M.D hanaffe loosu aana hossanno.

**Hawaasa, Dotteessa 25, 2013 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

የመንግሥት ሠራተኞችን በጊዜያዊነት ለመመደብ በወጣው ደንብ ቁጥር ፪/፳፻፲፪ መሰረት ተመድበው እየሰሩ ያሉ ሠራተኞች በጊዜያዊነት ተመድበው ባሉበት ተቋምና መደብ መስራታቸው የሚቀጥል ይሆናል፡፡

**፲ ተፈጻሚነት የሌለው ሕግና አሰራር**

፩ በክልል ማዕከል ተቋማት በነባሩ ዞን ሲሰሩ የነበሩ የመንግሥት ሠራተኞችን በጊዜያዊነት ለመመደብ የወጣ ደንብ ቁጥር ፪/፳፻፲፪ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፪ ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ለተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈጻሚነት የለውም፡፡

**፲፩ ደንቡ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከሚያዝያ ፳፭ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

ሀዋሳ፣ ሚያዝያ ፳፭ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**